የመከላከያ ሚኒስቴር
የአካል ስንኩን ማገገሚያ ክፍል

# ለቆሰለ ወታደር የሚሰጥ መረጃ

*መጽሃፉ የሚደርሰው ወንዶችን ነው፤ ሆኖም ለሁለቱም ጾታዎች የታሰበ ነው።

ሐምሌ 2018

**ለውድ ወታደር፣**

በመጀመሪያ እና ከምንም በላይ በቅርቡ ይሻልህ ዘንድና እና ጥሩ ጤንነት ይጠበቅልህ ዘንድ እንመኛለን። በመከላከያ ሚኒስቴር ስር ያለው የአካለ ስንኩል ማገገሚያ ክፍል ለአካለ ስንኩን 1959 ህግ እንደመሰረት ባገለገለውን የዴቪድ ቤን ጉሪኦን ራዕይ ላይ የተገፈ ለአይዲኤፍ አካለ ስንኩን አክብሮትን ፣ እውቅናና ቃል የሚገልጽና የሚሰጥ ብሔራዊ አንድነት ነው።
**የአይዲኤፍ አካለ ስንኩኖች እንዲያገግሙ እና ከማህበረሱ ጋር እንዲቀላቀሉ** የክፍሉ ሰራተኞች ይሰራሉ፤ ይህም ለአመቺ ተግባር ጥረት በማድረግ ረገድ እና የኤይዲኤፍ አካለ ስንኩን ድህንነታቸውን በማስጠበቅ የሚሰራ ስራ ነው። የክፍሉ ሰራተኞች ሙያዊ፣ ፈጣን እና ሰብአዊ አገልግሎት ለማቅረብ እና በቀጣይነት ለአገልግሎት መሻሻል በታማኝነት እየሰሩ ይገኛሉ።
የተለያየ ዘርፍ ባላቸው ሰራተኞችና ባለሙያዎች እንዲሁም በማገገሚያ ሰራተኞች (ማህበረዊ ሰራተኞች) ፣ ዶክተሮች፣ በደህንነት ሰራተኞች ፣በቅጥር ሰራተኖች እና በህክምና አገልግሎት ሰራተኞች ጭምር ለአይዲኤፍ አካለ ስንኩኖች አገልግሎቶች ይሰጣሉ። እነዚህ አገልግሎቶች በሰባት የማገገሚያ አውራጃዎች በሚከተሉት የሀገሪቱ ክፍሎች፡ ሄይፋ፣ ቲበሪአስ፣ ዳን፣ ቴል አቪቭ፣ ርሆቮት፣ ኢየሩሳሌም፣ ቤ’ ኤር ሼቫ እና በሁለት ቅጥያዎች፡ ኔታንያ እና ኢላት በሙሉ ይሰጣል።

ይህ አጭር መፅሃፍ በአካለ ስንኩን ህግ መሰረት ያለህን መብት ማግኘት እና መለማመድ የሚያስችልህን የሂደት መራጃን  ይሰጥሃል፤ እንዲሁም ስለ አገልግሎቶቹ፣ ብቃት እና ከአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ጋር መገናኘት ስለምትችልበት መንገድ እጥር ምጥን ያለ መረጃን ይሰጥሃል፡ ፡ ይህ አጭር መጽሀፍ ስለ መብትህ አና በመብትህ ዙሪያ ላሉህ የግንዛቤ መንገዶች አስተዋፅዎ እንደሚያደርግ ተስፋ እናደርጋለን።
ይህ አጭር መፅሃፍ የሚደርሰው ለወንዶች ቢሆንም ለሁለቱም ጾታዎች የታሰበ ነው።

**ስለ አካለ ስንኩን ማገገሚያ ቅርጫፍ ዝርዝር መረጃ ከሚከተለው ድህረ-ገጽ ማግኘት ይቻላል፡**
**www.shikum.mod.gov.il**

ለአንተ ምቾት ሲባል በሚውጡበት ከእሁድ እስከ ሀሙስ ድረስ 08:00–18:00 ባለው ሰአት ውስጥ, b 03-7776777 የስልክ መስመር የአካለ ስንኩን ክፍል የጥሪ ማዕከል ይሰራል።

ፈጣን ማገገም ከአክብሮት እና
አድናቆት ጋር እንዲሆንልህ እንመኛለን
የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ሰራተኞች

## ይዘቶች


**የይግባኝ ጥያቄ አቀራረብ  እና ብቁነት ምዘና ክፍል ................................ 4**

የአካለ ስንኩን ህግ ........................................ 4

የአካለ ስንኩን መብቶች በሌሎች ህጎች መሰረት ........................................ 4

የአይዲኤፍ የአካለ ስንኩን ዘማች ሆኖ ለመታወቅ የማመልከቻ ማስገባት ሂደት ........................ 5

**የሜዲካል ኮሜቴዎች ክፍል ................................................. 6**

**የሜዲካል አገልግሎቶች ክፍል ................................................ 6**

**የማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል ............................................... 7**

**የካሳ፣ ጥቅሞች እና ደህንነት ክፍል ......................................... 7**

የኤምቲአር ካሳ አይነቶች........................................ 8

**የህክምና ክትትል እየወሰደ ላለ ቁስለኛ ቤተሰቦች የሚሰጥ እርዳታ (የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል መምሪያ 84.04)................................... 9**

የሚተኩ የጉዞ ወጪዎች ........................................ 9

የሚተኩ የጉዞ ወጪ ኢኮኖሚያዊ ወጪዎች ........................................ 9

የሚተኩ የሆቴል ውስጥ ቆይታ ወጪዎች ........................................ 9

የሚተኩ የሞግዚት/ የሃላፊነት ተቀባይ ወጪዎች ........................................ 10

የሚተካ የቤተሰብ አባላት የባከኑ የስራ ቀናት ........................................ 10

**ከታች ያለው መረጃ የአይዲኤፍ ዘማች ሆነው የተገኙትን ቁስለኛ ግለሰቦች የመንከባከብ ስራን የሚሰራውን የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል የተዋቀረባቸውን ክፍሎች የሚያብራራ መግለጫ ነው።**

## የይግባኝ ጥያቄ አቀራረብ እና ብቁነት ምዘና ክፍል

### የአካለ ስንኩን ህግ

የስንኩን ማገገሚያ ክፍል በአካለ ስንኩን ህግ (ካሳ እና ማገገሚያ)፣ 1959 (በማጠቃለያው እትም) (እዚህ ዶክመንት: "አካለ ስንኩን ህግ") ላይ የሚተዳደር እና የሚሰራ ነው። በአካለ ስንኩን ህግ መሰረት **"አካለ ስንኩን ግለሰብ" ማለት የተሰናበተ ወታደር ሆኖ በአገልግሎቱ የተነሳ በስንኩንነት የተሰቃየ ወይም ቋሚ አገልጋይ ወታደር ሆኖ በስንኩንነት የተሰቃየ ነው።** "ስንኩንነት" መደበኛ ተግባርን የመከወን ችሎታ ማጣት ነው፤ ይህም አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ሊሆን ይችላል። የተሰናበተ ወታደር ወይም ቋሚ አገልጋይ የሆነ ወታደር **አገልግሎት በመስጠት ላይ እያለ ወይም በእነዚህ ምክኒያቶች፡** ቁስል፣ ህመም ፣ የህመም መክፋት የተነሳ የመደበኛ ተግባር የማድረግ ብቃት ማነስ ማለት ነው።

የይግባኝ ጥያቄ አቀራረብ እና ብቁነት ምዘና ክፍል ለአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል አመቺ በርን ይከፍታል። ይህ ክፍል ቁስለኛ ግለሰብ ለመለየት ማመለከቻ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአስፈላጊ የመረጃ ስብሰባ፤ በተባለው ክስተት እና ወታደራዊ የጦር ሃይል አገልግሎት መካከል ያለውን ክስተታዊ ግንኙነት ምርምር እና እስከ የኦፊሰር የስምምነት ውሳኔና ማስታወቂያ እና የሜዲካል ኮሚቴ ውሳኔ ማስታወቂያ እስከሚወጣ ድረስ ያለውን ሁሉንም የእውቅና ደረጃዎችን ይሸፍናል።

**በካሳ ኦፊሰር ዉሳኔ ላይ ያለ አቤቱታ፡** በካሳ ኦፊሰር በተደረገ በማንኛውም ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ግለሰብ በአካለ ስንኩን ህግ መሰረት አቤቱታውን በአቤቱታ ኮሚቴ ፊት ይዞ የመቅረብ ሙሉ መብት አለው። በውሳኔው ክፍል ላይ ጉዳዩ እንደተገለፀው የእውቅና ጥያቄውን በአካለ ስንኩን ህግ መሰረት ለሚያስገባ ግለሰብ የሚላክ ይሆናል።

### የአካለ ስንኩን መብቶች በሌሎች ህጎች መሰረት

- ስንኩንነቱ ያደረሰበት ንፁሃን አካል (ሁኔታ ያልሆነ) ከሆነ ለምሳሌ በትራፊክ አደጋ ቢሆን ከሁለት አንድኑን ይህም በአካለ ስንኩን ህግ መሰረት (ካሳና እና ማገገሚያ) የካሳና መብቶች **ወይም** በጉዳቶት ህግ መሰረት ያደረገ ካሳ መምረጥ ይቻላል።
- በንጹሃን የደረሰ ጥፋት በጉዳቶች ህግ ስልጣን መሰረት ከንጹሃን ካሳ ከተቀበለ በአካለ ስንኩን ህግ መሰረት ማንኛውንም የእውቅና እና ካሳን የማግኘት መብት **እንዳይገኝ እና ክፍያ እንዳይሰጠው** ያደርጋል። የተገባው አካል ማንኛውም አይነት ክፍያን ከአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ከተቀበለ ሁሉም ክፍያዎች ወደ ከአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ተመላሽ ከሆኑ በኋላ የንፁሃን ጉዳቶች ህግ መሰረት የንጹሃን ጉዳቶች ህግ መምረጥ እንዲቻል ይደረጋል።
- እንደማንኛውም ዜጋ ወታደሩ በብሄራዊ ኢንሹራንስ ህግ መሰረት የስንኩንነቱን እውቅና ይግባኝ የመጠየቅ መብት አለው።

# የአይዲኤፍ የአካለ ስንኩን ዘማች ሆኖ ለመታወቅ የማመልከቻ ማስገባት ሂደት

**ደረጃ ሀ፡** በሆስፒታሉ ከሚደረገው እንክብካቤ እና በሆስፒታሉ ውስጥ ባሉ ያካር (የቀድሞ ራም 2) ተወካዮች ጋር በትብብር ወይም የድንገተኛ ኦፊሰር (በአይዲኤፍ ውክልና) በተጓዳኝ ሆነው በአካለ ስንኩን ህግ መሰረት ጉዳት የደረሰበት አካል የእውቅና ጥያቄ ፎርም ይሞላል። ፎርሙን ከያካር ተወካዮች፣ ከድንገተኛ ኦፊሰር ወይም በፖሊስ ስር ካለው የደህንነት ኦፊሰር ወይም ከአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ድህረ-ገፅ ላይ በማውረድ መውሰድ ይቻላል። የተሞላው ፎርም ከሚስጥራዊ ክፍያ እንዳይከፈል ከሚያደርግ ፎርም እና አግባብ ከሆነና ከተሟላ የህክምና ዶክመንት ጋር ተያይዞ በያካር ተወካዮች ወይም የድንገተኛ ኦፊሰሮች በኩል በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ስር ወዳለው የይግባኝ ጥያቄ አቀራረብ እና ብቁነት ምዘና ክፍል የሚተላለፍ ይሆናል።

⬇

**ደረጃ ለ፡** የእውቅና ጥያቄው በይግባኝ ጥያቄ አቀራረብ እና ብቁነት ምዘና ክፍል ከደረስ በኋላ የድንገተኛ ኦፊሰር ለተጎዳው አካል በጉዳቱ ሁኔታ መሰረት ከሚከተሉት ይህም፥ የህክምና ክትትል ፈቃድ ብቻ፣ ጊዜያዊ ፈቃድ ወይም የተሻለ ዋጋ ባለው ከመታወቅ ፈቃድ አንዱን ፈቃድ እንደተሰጠው በፅሁፍ ይሳውቀዋል።

⬇

**ደረጃ ሐ፡** ከአይኢኤፍ የማቋረጫ ተወካዮች እና ከተጎዳው ግለሰብ (የቋሚ አገልግሎት የሰራተኞች ጉዳይ አስፈጻሚ ቢሮን ሳያጠቃልል) ጋር በመተተባበር ወታደሩ ከአይዲኤፍ ይሰናበታል።

⬇

**ደረጃ መ፡** ከአይዲኤፍ ስንብት በኋላ ለተጎዳው ግለሰብ እንዲሁም ለቤተሰቦቹ ክትትልና እንክብካቤ እርሱ በሚመድበት እና በድንገተኛ ኦፊሰር በተረጋገጠ ፈቃድ መሰረት በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል አውራጃ ይሰጣል፥

በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ስር በሆስፒታሉ ውስጥ እየታከመ ላለ ቁስለኛ የመገናኛ መንገድ አለ፥- ከያካር ተወካዮች እና የፖሊስ ደህንነት ኦፊሰሮች ጋር የምትገናኝ በሙያው የማህበረሰብ ሰራተኛ አለች። የእርሷ ስራ በሆስፒታሉ ቅስለኛው ውስጥ ክትትል በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ እርሱን መጎብኘት፣ እርሱንና ቤተቦቹን የመተዋወቅ እና ከቅስለኝነት ሁኔታ ሲወጣ የሚፈልጋቸውን ነገሮች መረዳት ነው። በተጨማሪም አካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል፣ የእውቅና ጥያቄ አቀራረብ ሂደት እና በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል በኩል የሚሰጥ ድጋፍን የተመለከተ መረጃን ማድረስ ይኖርባታል።

## የሜዲካል ኮሜቴዎች ክፍል

ጥያቄው በድንገተኛ ኦፊሰር የታወቀለት አካለ ስንኩን ግለሰብ የስንኩንነቱ መጠን ይታወቅ ዘንድ በህክምና ኮሚቴ ፊት እንዲቀርብ ይጋበዛል። በይግባኝ ጥያቄ አቀራረብ እና ብቁነት ምዘና ክፍል ውስጥ ለወጥ ወይም ጊዜያዊ ቆይታ በድንገተኛ ኦፊሰር የታወቀ የእያንዳንዱን ጉዳት መዳሰስ እና ለጉዳት መጠን ግምት የምርመራዎች ፋይል  አንቀፆች መሰረት የጉዳት በመቶኛ መግለፅ የሚዲካል ኮሚቴ ሚና ነው።
የሜዲካል ኮሚቴ አባላት በመከላከያ ሚኒስቴር የተሾመ ልዩ ባለሙያተኞች ናቸው። ውሳኔዎቹ በሜዲካል ማቴሪያል እና የቁስለኛውን ምርመራን መሰረት ያደረጉ ናቸው።
በክልላዊ ሜዲካል ኮሚቴው የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ ከፍተኛ የሜዲካል ኮሜቴ በአካለ ስንኩን ህግና መመሪያዎች ከተገለፀው ጋር የስምምነት መንገድ ላይ ከመድረሱ በፊት አቤቱታን መቅረብ ይችላል።
ከፍተኛ የሜዲካል ኮሚቴው ውሳኔውን የማጽደቅ፣ የማዘር እና የመቀየር ስልጣን አላቸው። የተጎዳው ግለሰብ ኮሜቴው ውስጥ ቢገባልኝ ይሆነኛል ብለው የሚያስበውን አካል ለምሳሌ ዶክተር፣ ኮማደር፣ ወላጅ እና ሌላም ማንኛውም ሰው ማስገባት ይችላል።
ቁስለኛው በሆስፒታሉ ውስጥ የአልጋ ቁረኛ በሚሆንበት ሁኔታ ወቅት ወይም በሜዲካል ኮሚቴ ፊት መቆም ሲያቅተው ኮሚቴው ስብሰባውን በሆስፒታሉ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ ያደርጋል።
የኮሜቴው ውሳኔ ላይ በክልላዊ ትሎት በአካለ ስንኩን ህግ እና መመሪያዎች ጋር በሚሄድ መልኩ በተለይ ደግሞ ህጋዊ ጉዳዮችን በተመለከተ አቤቱታን ሊቀርብ ይችላል።

## የሜዲካል አገልግሎቶች ክፍል

የሜዲካል አገልግሎቶች ክፍል አላማ ለአይዲኤፍ ስንኩን ዘማቾችን ተገቢ የሆነን የሜዲካል ክትትል ማዘጋጀት እና እንደገና ከቤተሰቦቻቸው፣ ከማህበረሰቡ እና ከቅጥር ጋር እንደገና መቀለቀል እንዲችሉ ማስቻል ነው።
በህክምና ስፍራ ክትትልን እያገኘ እያለ ከሶስቱ ፈቃድ አይነቶች ውስጥ አንዱን ፈቃድ ከይግባኝ ጥያቄ አቀራረብ እና ብቁነት ምዘና ክፍል ያገኘ (ከላይ ያለውን ተመልከት) እና ከአይዲኤፍ የተሰናበተ ወታደር በደረሰበት ጉዳት የተነሳ በሀገር ውስጥ ዶክተር ማረጋገጫ የሜዲካል ህክምና ይወስዳል። ህክምናው የሚከተሉትን ፡ የሆስፒታል ክትትል፣ የህክምና ምርመራዎች፣ መድሃኒት እና የሜዲካል ማሳሪያ፣ በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል መመሪያዎች የተገለጡጸት ወደ ህክምና ስፍራ ወይም ክትትል ሰጪ ተቋማቶች ትራንስፖርት አገልግሎት ያካትታል።
እነዚህ ክትትሎቹ በሁሉም የእስራኤል የታወቁ የሜዲካል ተቋማት እና በሀገር ውስጥ ዶክተር ውሳኔ መሰረት የሚሰጥ ይሆናል። በተጨማሪም ባለታሰቡ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የርቀት የሜዲካል ክትትል አስፈላጊነት ይመረመራል።
የታወቀ እና የስንኩንነቱ መጠን ምዘና 20% እና ከዚያ በላይ የተሰጠው ቁስለኛ ግለሰብ በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ለተለየበት ስንኩንነት የሜዲካል ክትትል የማግኘት መብት አለው። የስንኩንነቱ መጠን ምዘና ከ20% የቆሰለ ወታደር በብሔራዊ የጤና ኢንሹራንስ ህግ መሰረት የሜዲካል ክትትሉ በኤችኤምኦ በኩል ይሰጠዋል።

## የማገገሚያ አገልግሎቶች ክፍል

የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ዋና ተልዕኮው አካለ ስንኩን ግለሰቡን **ማገገም** እንዲች መርዳት ነው። በዚህም ተገቢ በሆነ መልኩ ቀጣይና አመቺ የስራ እድል ሁኔታን በመፍጠር ከማህበረሰቡ ጋር መቀላቀል እንዲችል ማድረግ ነው። ይህ ከስራው አለም ጋር መቀላቀሉ ለማህበረሰብ ህብረት እና የግል አስተሳሰብን በማዳበር ረገድ እንዲሁም ተጨማሪ ዘረፈ ብዙ ጉዳዮ`ች ላይ የበኩሉን አስተዋፅዖ ያበረክታል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ነው።
የስንኩንነት ደረጃቸው 20% እና ከዛ በላይ የሆነ የአይዲኤፍ አካለ ስንኩን ዘማቾች በማገገም ሂደት ላይ እርዳታን የማግኘት መብት አለው። እነዚህ እርዳታ፡ ሳይኮ-ሶሻል ቴራፒ፣ ምሪት እና ድጋፍ፣ የማገገሚያ ፕሮግራም ማዳበር እና መለየት ናቸው። የማገገሚያ ሰራተኞች (በሙያዎቸው የማህበረሰብ ሰራተኞች)፣ በተለያዩ የማገገሚያ አውራጃዎች ውስጥ ከአውራጃው የክትትል ቡድን ጋር እና ከአካለ ስንኩን ግለሰቡ ጋር በመተባበር የማገገሚያው ሂደት በትክክል እንዲቀጥል ይደረጋል። ለእያንዳንዱ የአይዲኤፍ አካለ ስንኩን ዘማች መሆኑን ለታወቀ ግለሰብ የማገገሚያ ሰራተኛ ይመደብለታል፤ እንዲሁም ሰራተኛው እንደ ኬዝ አስተዳዳሪ (ኬአ) ያገለግላል።
አብዛኛውን የግል እና ሙያዊ የማገገም ሂደቶች ውስጣዊና ውጫዊ ምንጮችን ለማጠናከር ክውኖችን ያካትታሉ። የእነዚህም ምንጮች ስኩንነቱን በመላመድ ከውስጡ የሚወጣውን ለመቀየር ይረዳሉ። የማገገሚያ ሰራተኞች እና የአውራጃው የሰራተኞች ቡድን አካለ ስንኩኑ በሚሰናበትበት ከማገገሚውያ ጋር በሚዛመድ ነገር ሁሉ ይገኛሉ። የማገገሚያ ሂደት ፕሮግራም በችሎታ፣ በሙያዊ ዝንባሌዎች፣ የታወቀውን የስንኩንነቱን ደረጃ በመድረስና በህጉ እና በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል መመሪየዎች ላይ በመመስረት የተደራጀ ነው።

## የካሳ፣ ጥቅሞች እና ደህንነት ክፍል

የክፍሉ ሰራተኞች የአካለ ስንኩን ግለሰቡ በደህንነት መስክ የህጉን ስልጣን ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሚቀየረው የክፍሉ መመሪያ ጋር አዛምደው ለግለሰቡ ይህንን በማስረዳት በህግ ዘንድ ደህንነትን የማስጠበቅ መብት እንዳለው መገንዘብ እንዲችል ይረዱታል። አካለ ጉዳተኛው ግለሰብ ባለመብት ለሆነባቸው ፍቃዶችን እና ተያያዝ አገልግሎቶችን በተመለከተ በአውራጃው ያሉ ሰራተኞች ስንኩኑ እንዚህን ጉዳዮ`ች እንደሚለያቸው ያሳውቁታል ደግሞም ይመሩታል፡ በአካል ጉዳት ምዘና 20% የጉዳት ደረጃ እና ከዛ በላይ የሆነ ስንኩን ዋና ወርሃዊ ካሳ የመውሰድ መብት አለው። የካሳው ደረጃ በጉዳቱ ደረጃ እና በህጉ እንደታዘዘው መሰረት የሚከፈል ይሆናል።. ብቻውን መቆም የሚችል ወታደር ተብሎ የተለየ ቁስለኛው ወታደር (በአይዲኤፍ ፍቃድ መሰረት) ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ የአንድ ጊዜ እድል ይሰጠዋል።

የህክምና ክትትል እየወሰደ የሚገኘው ቁስለኛው ግለሰብ ከሚከተሉት ጉዳዮ`ች ስር የሜዲካል ክትትል መመሪያ (ኤምቲአር) ካሳ ባለመብት ነው።

- በመመሪያው እውቅናን እና ከአይዲኤፍ መልቀቂያን መቀበል
- በአውራጃው ዶክተር የተፈቀደ
- በካሳ ኦፊሰር

## የኤምቲአር ካሳ አይነቶች

<u>የግዳጅ አገልግሎት በሆስፒታል ክትትል ስር ያለ ወታደር፥</u>- ከመመሪያዎቹ ጋር በመተባባር ከአይዲኤፍ ከተሰናበተበት ቀን አንስቶ ወርሃዊ ካሳውን ይቀበላል።

<u>ሪዘርቭ አገልግሎት በሆስፒታል ክትትል ስር ያለ እንደ ወርሃዊ ተከፋይ ተቀጣሪ ሆኖ የሚሰራ ወታደር፥</u>- ከአፋጣኝ የተልኮ ግዳጅ ከተሰናበተበት ቀን ጀምሮ ካሳ መቀበል ይጀመራል፤ በጣም በቅርቡ ከተመለመለበት ከ3 ወር ወዲህ ያለውን አማካይ ወረሃዊ ደሞዝ መጠን፤ በቋሚ ተቀያሪ ወታደር እንደተለምዶው ክፍያ ይሆናል።

<u>ሪዘርቭ አገልግሎት በሆስፒታል ክትትል ስር ያለ እንደ ቋሚ ሰራተኛ ሆነ የሚሰራ ወታደር፥</u>- ካሳው በባለፈው አመት የቅርብ የገቢ ታክስ ምዘና መሰረት ይወሰናል።

<u>ሪዘርቭ አገልግሎት በሆስፒታል ክትትል ስር ያለ ያልተቀጠረ ወታደር፥</u> - ከግዳጅ አገልግሎት የተሰናበተ ወታደር ከሚቀበለው ወርሃዊ ካሳ እኩል ይወስዳል።

በሚቀጥለው ምዕራፍ በፕሪንሲፕል የታወቀ በሆስፒታል ክትትል ስር ያለ ቁስለኛ ወታደር ቤተሰብ ያላቸውን መብቶች እንመለከታለን።

## የህክምና ክትትል እየወሰደ ላለ ቁስለኛ ቤተሰቦች የሚሰጥ እርዳታ (የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል መምሪያ 84.04)

**የሚተኩ የጉዞ ወጪዎች**

1. የአይቶቢስ ትራንስፖርት ወጪ በህዝብ ትርንስፖርት ተመን መሰረት ወይም የእስራኤል ባቡር ትራንስፖርት ተመን መሰረት የመልሶ ክፍያው የሚከፈል ይሆናል።
2. በቂ የአይቶቢስ መስመር "ያልተገደበ ጉዞ" ቲኬት ምርጫ ካለ እና ለአንድ ሰው ከ20 ጉዞዎች በላይ ከተፈቀደ- የመልሶ ክፍያው ተመን በ"ያልተገደበ ጉዞ" ቲኬት መሰረት ይከፈላል።
3. ለህዝብ ትራንስፖርት ወጪዎች የመልሶ ክፍያው ተመን በህዝብ አገልግሎት ሰራተኞች የጉዞ ወጪ በኪሎሜትር ላይ የተመሰረተ ነው።
4. በኢላት የሚኖሩ የቁስለኛው ቤተሰብ አባላት (ቁስለኛው ወታደር እዚህ ባለው የህክምና ስፍራ ከሌለ) የአየር ቲኬት እና ቲኬቱ የተከፈለበት ኦሪጅናል ደረሰኝ (ኦሪጅናል ብቻ) ከቀረበ የአየር በረራ የመልሶ ክፍያው ይቀበላሉ።
5. የገንዘብ የመልሶ ክፍያው በጉዳቱ ጥብቅነት ላይ ተሰርቶ ለተወሰኑ የቤተሰብ አባላት የሚሰጥ ነው።

**የሚተኩ የኢኮኖሚያዊ ወጪዎች**

1. የምትክ ክፍያ ተመኖች: መኖሪያ፣ የቁርስ፣ ምሳ እና እራት ከጊዜ ወደ ጊዜ ለህዝብ አገልግሎት ሰራተኞች በተወሰነው እንደምግቡ ተመን መሰረት የሚተካ ይሆናል።
2. የገንዘብ የምትክ ክፍያው በጉዳቱ ጥብቅነት ላይ ተመስርቶ ለተወሰኑ የቤተሰብ አባላት የሚሰጥ ነው፤

**የሚተኩ የሆቴል ውስጥ ቆይታ ወጪዎች**

የገንዘብ የምትክ ክፍያው በጉዳቱ ጥብቅነት ላይ ተስርቶ ለተወሰኑ የቤተሰብ አባላት የሚሰጥ ነው። የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ፈቃድ በመከተል የቁርስ እና የመኝታ ወጪዎች ሽፋን ከሁለት እንዱ ሁኔታ ላይ የሚዘጋጅ ይሆናል።

1. በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ፋይናንሻል ግዴታ።
2. በደረሰኙ መሰረት የገንዘብ መልሶ መክፈል የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ቅርንጫፋ ከሆቴሉ እና ቤተሰብ ሆቴል ለመቆየት ባወጡት ክፍያ ላይ ስምምነት ካላደረገ / በዚህ ሁኔታ ተመላሽ ገንዘብ ወደ አካለ ስንኩን ክፍል ተመን ውስጥ ገብቶ የሚተገበር ይሆናል።

**የሚተኩ የሞግዚት/ እንክብካቤ ሰጪ ወጪዎች**

1. የመልሶ ክፍያ የማግኘት መብት ያለቸው – የህክምና ክትትል የሚያስፈልጋቸው የቆሰሉ ወታደሮች ሆነው ልጅ ወይም ከ14 ዓመት በታች የሆኑ ወንድሞችና እህቶች ያላቸው ለሰአታት በአጋሮቻቸው ወይም ወላጆቻቸው ሲገበኙ።
2. ጉዳቱ ከደሰረበት ቀን ጀምሮ/ በሆስፒታል ውስጥ የህክምና ክትትል ማድረግ ከጀመረበት፣ የሚፈለገውን የጊዜ ገደብ በተመለከተ ከአውራጃው ተወካዮች ጋር ስምምነት ላይ ከተደሰረ በኋላ የሚተካ ክፍያው የሚሰጥ ይሆናል።
3. ወጪዎቹ በእንክብካቤ ሰጪ ደረሰኝ ወይም በቅስለኛው ወታደር አጋር ወይም ወላጅ በሚቀርብ መግለጫ መሰረት።
4. የሚተካው ክፍያ ከተወሰነው የሰአታዊ ስራ ተመን በላይ አይበልጥም።
5. የሚተካ ክፍያ የሚደረገው በሆስፒታል የህክምና ክትትል ወቅት የተነሳ ለሚጠየቀው ተጨማሪ ሰኣታት ብቻ የሚሆን እንጂ ለሁሉም የስራ ሰኣታት ቁጥር የሚደረግ አይደለም። **ማብራሪያ:** ቤተሰቡ በቤታቸው እንክብካቤ ሰጪው በቀን በተለምዶ ለ8 ሰአታት የሚሰራ ከሆነ እና ቀጣዮቹን 4 ሰአታት የተጎዳው ግለሰብ እንዲያገለግል የስራ ጫና ከተጨመረበት የመልሶ ክፍያው የሚሰጠው ለተጨመረው 4 የስራ ሰአታት ብቻ ነው።

**የሚተካ የቤተሰብ አባላት የባከኑ የስራ ቀናት**

በባከኑ የስራ ቀናት የተነሳ የባከነ ወይም የተቆረጠ ደሞዝ ክፍያ የሚፈቀደው በቤተሰቡ ውስጥ ከሉ አባላት ውስጥ ለአንዱ ብቻ የሚከተሉትን አራት ሁኔታዎች ሲሟሉ የሚሰጥ ይሆናል።

1. በአሰሪ የሚከተሉትን ያካተተ የጽሁፍ ማረጋገጫ፤
   - ቁስለኛው ወታደር የሆስፒታል ክትትል በሚያደርግበት ቆይታ ሁሉ የቤተሰቡ አባል አብሮት በመሆኑ ከስራ ቀሪ በመሆን የባከነውን ጊዜ የሚገልፅ ዝርዝር።
   - አስቀድሞ በተገለፀበት ወቅት ምንም አይነት ወርሃዊ ክፍያ ያለመከፈሉን ማረጋገጫ።
   - በአስቀድሞ ገለጻ ወቅት "የቤተሰብ አባል የህመም ክፍያ" ምንም ክፍ አለመከፈሉንና ይህም ለዚህ ክፍያ ምንም ጥያቄ አለመቅረቡን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ
2. በቤተሰብ አባል አስቀድሞ በተገለፀ የጹሁፍ መግለጫ ይህም ታማሚው በሆስፒታል ውስጥ አልጋ ይዞ የህክምና ክትትል በሚያደርግበት ጊዜ ሁሉ አብሮት ሆኖ እያስታመመ ለመቆየት መፈለጉን የሚገልፅ ሲሆን
3. አካለ ስንኩን ግለሰብ የህክምና ክትትል እያገኘ ባለበት የሜዲካል ጣቢያ ውስጥ የቤተሰቡ አባላት ዘወትር ከታካሚው መኘታ አጠገብ እንደሚገኙለት የሚያረጋግጥ የፅሁፍ ማረጋገጫ ከዲፓርትመንት አስተዳዳሪው መዘጋጀት ስለሚኖርበት ይህ ማረጋገጫ በጣም ወሳኝ ነው።
4. የህመምተኛ ፈቃድ / የእረፍት ጊዜ የመጠቀም ፈቃድ እና አሰሪ ፈቃድ ይህም በእነዚህ ቀናት ውስጥ ከአካለ ስንኩን ቅርጫፍ ከክፍያ ደረሰኝ በላይ ለሰራተኛው ዱቤን ሊሰጥ ካሰበ።

የባከኑ የስራ ቀናት የገንዘብ የመልሶ ክፍያ ጉዳት ከደረሰበት ቀን / በሆስፒታሉ ውስጥ ክትትል ማግኘት ከጀመረ ቀን እና በወሩ ካሉት ቀሪ ቀናት አንጻር አንስቶ ይቆጠራል። የባከኑ የስራ ቀናት የገንዘብ የመልሶ ክፍያ የቤተሰቡ አባላት ባቀረቡት ገቢ ፈቃድ መሰረት ይሆናል።

**የወጪዎች ተመላሽ ክፍያ የሚዘጋጀው በአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ፈቃድ እና ከሚከተሉት ስምምነቶች ጋር ነው፣**

1. የጉዳቱን አስከፊነት መግለፅ።
2. በህክምና ስፍራ ክትትል እያገኘ እያለ የቤተሰቦቹ አባላት በግለሰቡ መኝታ አጠገብ ለመቆየት የሚያስፈልጋቸው ቅድመ ሁኔታዎችን መግለጽ።
3. በሆስፒታሉ ሜዲካል ፈቃድ ላይ በመመስረት።
4. በቤተሰብ አባላት የተፈረመበት የተመላሽ ክፍያ ጥያቄ - ይህ አንቀጽ የትራንስፖርት፣ ኢኮኖሚ እና ለተጎዳው ወታደር ቤተሰቦች የመኝታ ወጪ ጉዳዮችን አጠቃሎ የሚይዝ ይሆናል።

- የሚፈቀድበት ቀን: ወታደሩ በአዲይዲኤፍ የግዳጅ / የሚጠበቅ አገልግሎት ከተሰናበተበት ቀን አንስቶ (ያልተሰናበተ እና እስከካሁን እያገለገለ ላለ ይህ ሃላፊነት የሚወስደው አይዲኤፍ ነው።) የቁስለኛው ቤተሰብ አባላት የሚወጣቸውን ወጪዎች ተመላሽ ክፍያ መስጠት የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል ሃላፊነት ነው።
- ብቁ የሆኑ ቤተሰብ አባላት: የመጀመሪያ ደረጃ የቤተሰብ አባላት (ሚስት/ ባል፣ አሳዳጊ ወላጆች፣ ወንድሞች እና እህቶች) በህክምና ስፍራ ክትትል እያገኘ ያለው ጉዳተኛ ጋር አብረው የሚያድሩ እና/ ወይም በተመደበ ሰአት እየመጡ የሚጎበኙ ናቸው።
- የተፈቀዱ የተመላሽ ክፍያዎች በተጎዳው ወታደር ካሳ ለአካለ ስንኩን ክፍል ዝርዝረ መረጃ ወደገባ ባንክ አካውንት የሚገባ ይሆናል።
- የቋሚ አገልግሎት አርሚ ሰራተኞች ጉዳይ ቢሮ የቤተሰብ አባላት የስራ ቀናት እና የሞግዚት ወጪዎች ተመላሽ ክፍያን ማድረግ ብቻ ነው የሚመለከተው።

የመከላከያ ሚኒስቴር
የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ክፍል

የአካለ ስንኩን ማገገሚያ ዋና ክፍል፣ 94 ጃቦቲንስካይ ሴንት ፕታች ቲክቫ
የድህረ-ገፅ አድራሻ: www.shikun.mod.gov.il